ኢ ዴ አ ፓ - መ ድ ኅ ን
U E D P - M E D H I N
Head Office ☐ Branch Office ☐ Support Group ☐

ቀን 7/8/2000 ዓ.ም
Date
ቁጥር ኢ-መ 087/2000
Ref.

# ከኢዴአፓ-መድህን የተሰጠ መግለጫ

ትናንት ሚያዝያ 6 ቀን 2000 ዓ.ም በሁለት የአዲስ አበባ ከተማ አካባቢዎች በደረሰ የፈንጅ ፍንዳታ በርካታ ንፁሃን ዜጐች ላይ የሞትና የመቁሰል አደጋ መድረሱን በዛሬው እለት ከመንግሥት የመገናኛ ብዙሃን አድምጠናል፡፡

በሰላማዊና የእለት ተዕለት እንቅስቃሴ ላይ በነበሩ ሲቪል ዜጐች ላይ እንዲህ አይነት አሰቃቂ የሕይወትና የአካል ጉዳት በመድረሱ ፓርቲያችን ኢዴአፓ-መድህን የተሰማውን ልባዊ ሃዘን እየገለፀ፣ ይህ አይነቱ የሽብር ተግባር በማንኛውም ምክኒያት ሆነ በማንኛውም አካል መፈፀሙን ኢዴአፓ-መድህን አጥብቆ ያወግዛል፡፡ በተለይም ይህ የሽብርተኝነት ተግባር በምርጫ ወቅት መፈፀሙ በአገራችን የወደፊት የዴሞክራሲያዊ ሂደት ላይ ከፍተኛ አሉታዊ ጫና የሚያስከትል በመሆኑ - ድርጊቱን ሰላምና ዴሞክራሲ በአገራችን እንዲሰፍን የሚፈልግ አገር ወዳድ ዜጋ ሁሉ አጥብቆ ሊያወግዘው ይገባል ብሎ ፓርቲያችን ኢዴአፓ-መድህን በፅኑ ያምናል፡፡

የሕዝቡን ሠላምና ደህንነት የማስጠበቅ ቀዳሚ ኃላፊነት ያለበት መንግሥትም ትክክለኛ የሽብር ተግባር ፈፃሚ የሆኑትን አካላት ተከታትሎ ለፍርድ የማቅረብና - ከተመሳሳይ የሽብር አደጋ ህብረተሰቡን የመጠበቅ ኃላፊነቱን በአግባቡ እንዲወጣ ፓርቲያችን በዚህ አጋጣሚ ያሳስባል፡፡

ሠላምና ህብረ-ብሔራዊነት ዓላማችን ነው!
የኢዴአፓ-መድህን ስራ-አስፈፃሚ ኮሚቴ
አዲስ አበባ
ሚያዝያ 7 ቀን 2000 ዓ.ም

Head Office Addis Ababa ☎ 50 87 27 / 50 87 28 ✆ 50 87 30 ✉ 101458 E-mail:addisedepa@hotmail.com
Our Account No. Addis Ababa, Bank of Abyssinia Filwuha Branch A/C 145
Branch Office or Support Group in ______ Tel: ______ Fax: ______ P.O.Box: ______
E-mail: ______